**ሳምንታዊ ዜና ዘገባ**

**ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ራዲዮ የካቲት 28 ቀን 2001 ዓ.ም.**

- **የወያኔ ካድሬዎች በፈጠሩት ተንኮል የባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች እርስ በርስ ተጋጩ፣**
- **በርካቶች በፌደራል ፖሊስ ተደብድበዉ ሆስፒታል ገብተዋል፣**
- **የአባ ጳዉሎስ ቀኝ እጅ የሆኑት አቡነ መልከፀዲቅ እጅግ ዘመናዊ መኪና በ1.3 ሚለዮን ብር ተገዝቶ ተሰጣቸዉ፣**
- **የወያኔ የፌደራል ፖሊስ ባለስልጣን ስርዓቱን ከድቶ ኮበለለ፣**
- **የሱዳን እና የወያኔ ምስጢራዊ ስምምነት ሰሞኑን ተጠናቀቀ ተባለ፣**

**ዘርዝሩን በሚቀጥለዉ ገፅ ያገኙታል <<<>>>**

*በባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ግቢ ውስጥ በተከሰተ ብጥብጥ በርካታ ተማሪዎች ተጎድተው ሆስፒታል ሲገቡ በርካቶች ታፍሰው ለእስር መዳረጋቸው ታወቀ::*

*ማክሰኞ የካቲት 17 ቀን 2001 ዓ.ም. ምሽት ላይ በተማሪዎች እና በግቢው ጥበቃ ሰራተኞች የተጀመረው ፀብ ወደ ግቢው ተማሪዎች ዘልቆ ገብቶ እርስ በርስ በድንጋይ እና በዱላ ከመደባደባቸውም በላይ ችግሩን እቀርፋለሁ ብሎ ወደ ግቢው የገባው የፌዴራል ፖሊስም በተማሪዎቹ ላይ ዘግናኝ ድብደባ መፈፀሙ ታውቆዋል::*

*በጥበቃ ሰራተኞች እና በሁለት ተማሪዎች መሀከል የተጀመረውን የግል ፀብ የጥበቃ ሰራተኞቹ በፈጠሩት ሀሰተኛ ምክንያት ተማሪዎቹ ያላሉትን በማለት ፀቡ ሳይታሰብ በተማሪዎቹ ዘንድ ቁጣ ቀስቅሶ በዱላና በድንጋይ እርስ በርስ ሲፋለሙ እንዳመሹና በማግስቱም የካቲት 18 ቀን 2001 ዓ. ም. ግጭቱ ተባብሶ ቀጥሎ እንደዋለ ከባህርዳር የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::*

*በአጭሩ ሊቀጭና ሊቀረፍ የሚችለውን ፀብ የወያኔ ሰላይ ጥበቃ ሰራተኞች ሆን ብለው ተማሪዎቹ እርስ በርስ እንዲጋጩ በማድረጋቸው ለሁለት ተከታታይ ቀናት ግጭቱ የቆየ ሲሆን በሁለቱ ቀናት ከ50 በላይ ተማሪዎች ቀላልና ከባድ የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸው ወደ ሆስፒታል ገብተው እንደነበረ የገለፀው ይሔው የደረሰን ዘገባ በተለይ 15 ተማሪዎች ከባድ ድብደባ የደረሰባቸው በመሆኑ በሆስፒታሉ ውስጥ ለቀናት ያህል ተኝተው ህክምና ሲደረግላቸው እንደሰነበቱ ዘገባው አስረድቷል::*

*የመርጃ መሳሪያ በሌለበት የቤተ መፅፍቱ ባልተሙዋላበት ሁኔታ ሁሉን ችለው በመማር ላይ ያሉትን ተማሪዎች የወያኔ መሰሪ ቡድን ጭር ሲል አልወድም በሚል እርስ በርስ እንዲጋጩ በተላላኪ ጆሮ ጠቢ የጥበቃ ሰራተኞች አማካኝነት ፀቡን ቀስቅሰው ከማደባደባቸውም በላይ ቅልብ የፌዴራል ፖሊሶችም በዩኒቨርስቲው ግቢ ውስጥ ገብተው ወንዱን ብልቱን ሴቱዋን ሆዱዋን እየመቱ ለከፍተኛ ጉዳት የዳረጉዋቸው ሲሆን ሆስፒታል ውስጥ ተኝተው የታከሙትም ቢሆን በፌዴራል ፖሊሶች ድብደባ የደረሰባቸው ተማሪዎች መሆናቸውንም ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል::*

*የካቲት 18 ቀን ጀምሮ እስከ የካቲት 24 ቀን 2001 ዓ. ም. ድረስ ለአንድ ሳምንት ያህል ትምህርት ተቋዋርጦ እንደነበረና በግቢው ውስጥ ሰፍሮ ከሰነበተው የፌዴራል ፖሊስ በተጨማሪ 5 አውቶቡስ የፌዴራል ፖሊሶች ከአዲስ አበባ መጥተው በግቢው የሰፈሩ በመሆኑ ተማሪዎቹ በሁኔታው በመደናገጥ ወደ የቤተሰቦቻቸው ለመሄድ እንደተገደዱም ዘገባው አብራርቶዋል::*

*የፌዴራል ፖሊስ ከ200 በላይ ተማሪዎችን አፍሶ ለ5 ቀናት ካምፕ ውስጥ ያጎራቸው ሲሆን ይህ ዘገባ እስከተጠናቀረበት ዕለት ድረስ ሁለት ተማሪዎች በእስር ላይ እንደሆኑ የደረሰን ዘገባ አጋልጦዋል::*

የባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት ዶክተር የሺ መርሻ በተባለችው ካድሬ ውሳኔም በርካታ ተማሪዎች ከትምህርታቸው ላይ እንዲባረሩ የተደረጉ ሲሆን በተለይ 5 ተማሪዎች ሙሉ ለሙሉ ከትምህርት ዓለም እንዲሰናቱ 10 ተማሪዎች ለአንድ ዓመት ሌሎች 10 ተማሪዎችም ለሁለት ዓመት ከትምህርታቸው እንዲታገዱ መወሰኑዋ ታውቆዋል::

በዚህ ውሳኔ የተበሳጬት የዩኒቨርስቲው ተማሪዎች በግቢው ውስጥ የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ሙከራ ያደረጉ ቢሆንም በግቢው ውስጥ ሰፍሮ ባለው የፌዴራል ፖሊስ አማካኝነት ሊከሽፍ እንደቻለ ዘገባው አስረድቶዋል::

:

የወያኔው ነፍስ አባት የአባ ጳውሎስ ቀኝ እጅ እንደሆኑ የሚነገርላቸው አቡነ መልከፀዲቅ የካቲት 9 ቀን 2001 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ደሳለኝ ሆቴል ውስጥ በተዘጋጀው የእራት ግብዣ ላይ በ1.3 ሚሊዮን ብር የተገዛ መኪና ቁልፉ እንደተበረከተላቸው ታውቆዋል::

ህዝበ ክርስቲያን ለእምነቱ ማስፋፊያና ለካህናቱ ደመወዝ ይሆን ዘንድ ብሎ በየደብሩ የሚያበረከረተውን ገንዘብ እያሰባሰቡ በግል የሂሳብ ደብተራቸው የሚከቱት እነ አባ ጳውሎስ ይሄ አልበቃ ብሎዋቸው ባለሀብቶች ሸለሙን በሚል ሀሰተኛ ምክንያት ከቤተክርስቲያኑዋ ወጪ በማድረግ ተገዝቶ እንደተሰጣቸው ምንጮች አጋልጠዋል::

በደቡብ ክልል ከተመደቡ ከ10 ዓመት በላይ ያለፋቸው አቡነ መልከፀዲቅ አባ ጳውሎስ አድርጉ የሚሉዋቸውን የሚያደርጉ ከመሆኑም በላይ ህዝበ ክርስቲያን ተቸግሮ ለቤተክርስቲያን የሚሰጠውን ገንዘብ ከሙዳየ ምጽዋቱ ላይ እየራገፉ የሚልኩላቸው መሆኑን ምንጮቹ አስረድተዋል::

አቡነ መለልከፀዲቅ የአርባ ምንጭ ከተማ የቅዱስ ገብርኤልና ቅዱስ ሚካኤል ደብር አስተዳዳሪን በየቤተክርስቲያኑ ሙዳየ ምጽዋት ውስጥ ያለውን ዘርግፈህ አምጣ ወይም በአባ ጳውሎስ የግል ሂሳብ ላይ ገቢ አድርጉ ተብሎ ትዕዛዝ ቢሰጣቸውም እምቢ በማለታቸው ለሁለት ወራት ያሳሰሩዋቸው መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ አስተዳዳሪውን ፍርድ ቤት በነፃ ቢያሰናብታቸውም ከአባ ጳውሎስ ጋር በመሻረክ ልዩ ትዕዛዝ ለከተማው ፖሊስ ተሰጥቶ ለሁለት ወራት ያለምንም ወንጀል እንዲታሰሩ ያስደረጉ መሆናቸውንም ዘገባው ገልፆዋል::

ዛሬ በየገጠሩ የሚገኙ ቤተክርስቲያናት እና ገዳማት ከዕድሜ ባዛት እየፈራረሱ ባለበት ፤መነኮሳት ተርበውና ታርዘው የሚያስታውሳቸው አጥተው በያሉበት እየሞቱ ባሉበት በዚህ ወቅት የወያኔ ሹመኛ ጳጳስ ለሆኑት አቡነ መልከፀዲቅ የ1.3

ሚሊዮን ብር ዘመናዊ መኪና ገዝቶ መስጠት የእምነቱን ተከታዮች እንዳስቆጣም ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

በህዝብ ላይ የፈፀመው ግፍና ስቃይ ያባነነው የወያኔው የፌዴራል ፖሊስ ከፍተኛ ባለስልጣን ስርዓቱን ከድቶ መኮብለሉን ከፌዴራል ፖሊስ ምንጮች ያገኘነው ጥቆማ ገለፀ፡፡

ከ1978 ዓ.ም. ጀምሮ ከወያኔ ጋር ተቀላቅሎ ሲንቀሳቀስ የነበረው ሻለቃ ሁሴን ዑስማን የተባለው የአፋር ብሔር ተወላጅ ስርዓቱን ከድቶ ወደ ጎረቤት ሀገር እንደተሰደደ የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ ገልፆ ምናልባትም ኬንያ ወይም ኤርትራ ሳይገባ እንዳልቀረ ጠቁመዋል፡፡

ከ23 ዓመት በላይ በወያኔ ቡድን ውስጥ ታቅፎ በህዝብ ላይ በደል እና ግፍ ሲሰራ የኖረው ሻለቃ ሁሴን ዑስማን የተባለው ግለሰብ የፌዴራል ፖሊስ የአንድ ብርጌድ አዛዥ ሆኖ ሲያገለግል የነበረ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ በተለይ ከአፋር ክልል ህዝብ ላይ የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት ከክልሉ አስተዳዳሪዎች ጋር በመመሳጠር በጀቱን እንደሚመዘብሩበት አጥብቆ ይገልፅ እንደነበረም ምንጮቹ አስረድተዋል፡፡

የወያኔ የጦር አዛዦች የሆኑት እነ ሳሞራ የኑስ ፤ታደሰ ወረደ፤ ሰዓረ መኮንን፤እና ሌሎችም ለክልሉ ምንም አይነት ግብር ሳይከፍሉ የጨው ምርት ማምረቻ ቦታ በነፃ ከእስማኤል አሊሴሮ ተሰጥቶዋቸው እያፈሱ እየሸጡ መሆናቸውን በግልፅ ይናገር እንደነበረ የጠቆሙት ምንጮች የፌዴራል ፖሊስ ባለስልጣናትም ከህዝቡ ላይ የሚመዘብሩት ሀብት እንዳለ በመናገሩ ለወራት እስር ቤት ታስሮ እንደነበረም ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በደቡብ ምዕራብ ዞን ጅማ ከተማ ማዘዣውን ያደረገው የፌዴራል ፖሊስ ብርጌድ አዛዥ የሆነው ሻለቃ ሁሴን ዑስማን ለ23 ዓመታት ከወያኔ ጋር ከበረሀ ጀምሮ ሲታገል የመጣ ቢሆንም በወያኔ ውስጥ ባለው አድልዖ ይበሳጭ እና ይናደድ እንደነበረ የገለፁት ምንጮቹ በማዕረግ አሰጣጡም ቢሆን ከፍተኛ በደል እንደደረሰበት ጨምረው አስረድተዋል፡፡

ወያኔ በህዝብ ላይ ከሚያደርሰው መከራና ስቃይ በተጨማሪ ምሽት ላይ በሚፈልጋቸው ግለሰቦች ላይ የግድያ እርምጃ በድብቅ እንዲወስዱ ትዕዛዝ እንደሚሰጣቸው ያጋለጡት የፌዴራል ፖለስ ምንጮች ይህንን ትዕዛዝ አንቀበልም ያሉ በርካታ ፖሊሶች ስርዓቱን ከድተው ግማሾቹ ወደ ውጭ ሀገር የኮበለሉ ሲሆን የተቀሩት ወደ ተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በመሄድ እየተደበቁ መሆኑን ምንጮቹ አብራርተዋል፡፡

በተለይ በአሁኑ ሰዓት ነባር የተባሉት የፌዴራል ፖሊስ አባሎች በሚደርስባቸው የተለያየ ጫና ምክንያት ስርዓቱን እየከዱ ከመሆኑም ሌላ በይፋ ስራ መልቀቂያ እስከ መጠየቅ ድረስ እንደደረሱ ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል።

ባለፈው ሳምንት በድብቅ በሁርሶ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ ውስጥ ለ6 ወራት ሲያሰለጥናቸው የነበሩትን በሺህዎች የሚቆጠሩ የፌዴራል ፖሊሶችን ያስመረቀ ሲሆን የሚከዱትና ስርዓቱን ጥለው የሚኮበልሉትም በተመሳሳይ በርካታ መሆናቸውንም ምንጮቹ ጨምረው አስረድተዋል።

የወያኔና የሱዳን መንግስት አዲስ ምስጢራዊ ስምምነት ማድረጋቸውን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ሾልኮ የደረሰን ዘገባ ገለፀ።

በሶስት ምዕራፍ የተከፈለው የወያኔና የአልበሽር ምስጢራዊ ስምምነት በርካታ ነገሮችን ያካተተ ቢሆንም መሰረታዊው የአልበሽር በዓለም አቀፉ ፍርድ ቤት መከሰስ እና የእስር ማዘዣ ወረቀት መቆረጡ እንደሆነ የገለጣ የደረሰን ዘገባ ሌሎቹም ስምምነቶች የሁለቱን ቡድኖች ጥቅም ሊያስጠብቁ ይችላሉ የተባሉ እንደሆነም ዘገባው አስረድቶዋል።

በሶስት ምዕራፍ የተከፈለው የወያኔና የአልበሽር ስምምነት መብራት ከሀገር ውስጥ ሰጥቶ ነዳጅ መቀበል፤ በድንበር ላይ ያሉትን የወያኔ ተቃዋሚ ኃይሎችን በጋራ ማስወገድ ፤የሁለቱ ሀገራት ተፈላጊ ሰዎች ወደ የሀገሮቻቸው ሲመጡ አሳልፈው መስጠት ፤ደህንነቶቻቸው ድንበር እየተሻገሩ እንደልባቸው እንዲሰሩ እና በጎንደር በኩል ተቆርሶ ለሱዳን የተሰጠው መሬት በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና እንዲያገኝ በጋራ ለመስራት መሆኑን ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል።